የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ
# ADDIS NEGARI GAZETA
OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

ሰላሳ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፹፰
አዲስ አበባ ሰኔ ፳፩ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ/ም

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

32th Year No.88
Addis Ababa 28th day of Jun, 2024

ማውጫ

ደንብ ቁጥር፻፸፰/፪ሺ፲፮
የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ባለሙያዎች የደንብ ልብስ አለባበስ የአፈፃፀም ደንብ
ገፅ……………………..…………………….፫ሺ፯፻፴፱

CONTENTS

REGULATION No. 178/2024
REGULATION ISSUED TO PERFORMING THE UNIFORM DRESS OUT OF EXPERTS WORKING IN HOTELS AND SIMILAR SERVICE PROVIDER INSTITUTIONS IN ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION
Page …………………..……………………. 3739

## ደንብ ቁጥር፻፸፰/፪ሺ፲፮

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ባለሙያዎች የደንብ ልብስ አለባበስ የአፈፃፀም ደንብ

በሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ውስጥ ለሚሰሩ ባለሙያዎች ወጥ የሆነ የአለባበስ፣ የጌጣጌጥ እና የመዋቢያ አጠቃቀም ሥርዓት በመዘርጋት የሀገር ባልህና እሴት እንዲጠበቅ ለማድረግና በዘርፉ ተሰማርተው የሚሰሩ ሙያተኞች ሊደርስባቸው ከሚችለው አካላዊ፣ ሥነ-ልቦናዊ ጫና እና አላስፈላጊ ጥቃቶችን ለመከላከል እና ዓለም አቀፍ መስፈርትን የሚያሟላ እንዲሆን ማድረግ በማስፈለጉ፣

## REGULATION No. 178/2024

## REGULATION ISSUED TO PERFORMING THE UNIFORM DRESS OUT OF EXPERTS WORKING IN HOTELS AND SIMILAR SERVICE PROVIDER INSTITUTIONS IN ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION

**WHEREAS,** it has become necessary to the standard dress out, use of jewelry and cosmetics by establishing a system for experts working in hotels and similar service provider institutions, in order to protect the values and cultures of the country and the experts working in the field can reach it to prevent physical, psychological pressure and unnecessary attacks and by requiring it to meet the international criteria;

ያንዱ ዋጋ
Unit price

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፪ሺ፬፻፵፭
Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445

በከተማችን በሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ወጥ የሆነ የአለባበስ ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ

የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፹፬/፪ሺ፲፮ አንቀፅ ፺፫ መሰረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ**

**፩ አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ባለሙያዎች የደንብ ልብስ አለባበስ የአፈፃፀም ደንብ ቁጥር ፻፸፰/፪ሺ፲፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪ ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ

፩ **"ከተማ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤

፪ **"አስተዳደር"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፫ **"አዋጅ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፹፬/፪ሺ፲፮ ነው፤

፬ **"ቢሮ"** ማለት አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የባህል፣ ኪነ-ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ነው፤

**WHEREAS,** it has become necessary to establish similar standard dress out procedure in hotels and similar service provider institutions in our city;

**NOW, THEREFORE,** this regulation is issued by the Cabinet of Addis Ababa City Government in accordance with the Addis Ababa City Government Executive Organs Establishment and to Re-specify the Power and Duties of the thereof Proclamation No. 84/2023.

**PART ONE**

**GENERAL PROVISIONS**

**1. Short Title**

This regulation may be cited as “Regulation issued to Performing the Uniform dress out of Experts working in Hotels and Similar service Provider Institutions in Addis Ababa City Administration Regulation No. 178/2024’’.

**2. Definition**

In this regulation, unless the context otherwise requires:

1. “**City**” mean the city of Addis Ababa;
2. “**Administration**” mean Addis Ababa City Administration;
3. “**Proclamation**” shall mean the Addis Ababa City Government Executive Organs Establishment and to Re-specify the power and duties of the thereof Proclamation No. 84/2023;
4. "**Bureau**" shall mean the Addis Ababa City Administration of Culture, Arts and Tourism Bureau;

፭. "**ጽህፈት ቤት**" ማለት የክፍለ ከተማ ወይም የወረዳ የባህል፣ ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ጽህፈት ቤት ነው፤

፮. "**የደንብ ልብስ" ማለት** በሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ሙያ ላይ ተሰማርተው የሚሰሩ ባለሙያዎች የሚለብሷቸው የደንብ ልብሶች፣ የሚጠቀሙባቸው መዋቢያዎች እና ጌጣጌጦች ናቸው፤

፯. "**የቱሪስት ታክሲ አገልግሎት አሽከርካሪ**" ማለት እንግዶችን ከአየር መንገድ ወደ ሆቴል እንዲሁም ከሆቴል ወደ አየር መንገድ እና ወደ ተለያዩ መዳረሻ ቦታዎች በራሱን ወይንም ተቀጥሮ በሚሰራበት የቱሪስት ታክሲ አገልግሎት የሚሰጥ ግለሰብ ነው፤

፰. "**የድጋፍና ክትትል ባለሙያ**" ማለት በዚህ ደንብ መሠረት አገልግሎት ሰጪዎች ህግን ተከትለው ስለመፈጸማቸው እንዲከታተልና የሙያ ድጋፍ እንዲያደርግ በቢሮው ወይም በጽህፈት ቤቱ የሚመደብ ባለሙያ ነው፤

፱. "**የኢንስፔክሽን ሥራ**" ማለት ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ለሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በዚህ ደንብ መሠረት እየሰሩ መሆናቸውን የመቆጣጠርና የማረጋገጥ ሥራ ነው፤

፲. "**ተንቀሳቃሽ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት**" ማለት በጎዳናና በተለያዩ ኩነቶች ላይ የምግብና የመጠጥ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማትና ግለሰቦች ናቸው፤

**5.** "**Office**" shall mean the Sub City or District Office of Culture, Arts and Tourism;

**6.** "**Uniform**" shall mean hotel and similar service provider institutions working uniforms worn by experts, cosmetics and jewelleries they are used;

**7.** "**Tourist Taxi Service Driver**" shall mean an individual that transport guests from the Airline to Hotel as well as from Hotel to Airline and to various destinations by his own self or self-employed tourist taxi service provider;

**8.** "**Support and Monitoring Experts**" shall mean the service providers under this regulation follow the law and provide professional support assigned by the Bureau or the Office;

**9.** "**Inspection Work**" shall mean it is the work of control and verification in cooperation with stakeholders for hotel and service provider institutions are working according to this regulation;

**10.** "**Mobile Service Provider Institutions**" shall mean institutions and individuals that provide food and beverage services on the street and at various events;

፲፩ **"መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ አገልግሎት ሰጪ አካላት"** ማለት በሶሻል ኮሚቴ፤ በማህበራት፤ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ውስጥ የምግብ፤ የመጠጥ፤ የመዝናኛ፤ የመኝታና መሰል አገልግሎት የሚሰጡ ናቸው፤

፲፪ **"ሆቴል"** ማለት የመኝታ፤ የምግብ፤ የመጠጥና እንደ አስፈላጊነቱም የመዝናኛ፤ ስብሰባና መሰል አገልግሎቶችን ለቱሪስቶችና ለሌሎች ተጠቃሚዎች የሚያቀርብ ድርጅት ነው፤

፲፫ **"መሰል አገልግሎት"** ማለት ሆስቴል፣ ሆቴል አፓርትመንት፣ ሎጅ፣ ሪዞርት፣ ሞቴል፣ እንግዳ ማረፊያ፣ ፔንሲዮን፣ ሥጋ ቤት፣ ቁርስ ቤት ወይም ካፌ፣ የፈጣን ምግብ ወይም ቴክ አዌይ መሸጫ፣ ላውንጅ፣ ምሽት ክበብ፣ ባርና ሬስቶራንት፣ ምግብ ቤት፣ ግሮሰሪ፣ ሳውናና ስቲም ባዝ፣ ማሳጅ፤ የበጋ ቤቶች፣ የካምፕ አገልግሎት፣ ዓለም አቀፍ ይዘት ያላቸው ምግብ ቤቶች፣ የምግብ፤ የመጠጥና የመዝናኛ አገልግሎት የሚሰጡ የስብሰባ ማዕከላት፣ የቱሪስት መኪና አከራዮች፣ የቱሪስት ታክሲ አገልግሎት፣ የባህላዊ መጠጥ ቤት፣ የጀበና ቡና እና የቴክ አዌይ አገልግሎት መስጫ ተቋማትን ያካትታል፤

፲፬ **"ሞቴል"** ማለት የምግብ፤ የመጠጥ፤ የመዝናኛ፤ የመኝታ፤ የመኪና ማቆሚያ፤ የመኪና ማጠቢያ፤ የጋራዥ አገልግሎት እና የመሳሰሉትን የሚሰጥ ድርጅት ነው፤

**11.** "**Governmental and Non-Governmental Service Providers**" shall mean they provide food, drinking, entertainment, sleeping and similar services in social committee, in associations, in governmental and non-governmental institutions;

**12.** "**Hotel**" shall mean an organization that providing sleeping, food, drinking and entertainment as needed meeting and providing similar services to tourists and other users;

**13.** "**Similar Service**" shall includes hostel, hotel apartment, lodge, resort, motel, guest house, pension, butcher, breakfast house or cafe, fast food or take away shop, lounge, night club, bar and restaurant, restaurant, grocery store, sauna and steam bath, massage, summer houses, camping Services, restaurants with international content, food, drinking and convention centres providing entertainment services and tourist car rentals service provider institutions;

**14.** "**Motel**" shall mean an organization that provides food, drink, entertainment, lodging, parking, car wash, garage service, etc.;

፲፭ "**ሆቴል አፓርትመንት**" የመኝታ፣ የምግብ፣ የመጠጥና እንደ አስፈላጊነቱም የመዝናኛ፣ ስብሰባና መሰል አገልግሎቶችን ለቱሪስቶችና ለሌሎች ተጠቃሚዎች የሚያቀርብ ሆኖ እንግዳው በራሱ ክፍል የራሱን ምግብ የሚያበስልበት ተቋም ነው፤

፲፮ "**ሥጋ ቤት**" ማለት ሥጋ ጨምሮ የመጠጥና የምግብ አገልግሎት የሚሸጥበት ተቋም ነው፤

፲፯ “**መጠጥ**” ማለት የአልኮልና አልኮል ነፃ መጠጦች ሲሆኑ አልኮል ነፃ ደግሞ ቡናን ጨምሮ ትኩስና ቀዝቃዛ መጠጦች ናቸው፤

፲፰ "**ግሮሰሪ**" ማለት አልኮልና አልኮል ያልሆኑ መጠጦችን አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ነው፤

፲፱ "**ሪዞርት**" ማለት የመኝታ፣ የምግብ፣ የመጠጥና እንደ አስፈላጊነቱም የመዝናኛ፣ ስብሰባና መሰል አገልግሎቶችን ለቱሪስቶችና ለሌሎች ተጠቃሚዎች የሚያቀርብ ሆኖ በአቅራቢያው የቱሪስት መስዕብ ያለው ነው፤

፳ "**ላውንጅ**" ማለት በምሽት የሚከፈቱ የመዝናኛ ቦታዎች ሆኖ በባንድ በሙዚቃ ወይም በዲጄ ሙዚቃ የሚቀርብበት እና የመጠጥ አገልግሎት አልፎ አልፎም የምግብ አገልግሎት የሚያቀርብ ተቋም ነው፤

፳፩ "**እንግዳ ማረፊያ**" ማለት ሣሎን፣ መኝታ ቤት፣ የምግብ ማዘጋጃ፣ መታጠቢያ ክፍሎች፣ እንዲሁም የቤት ዕቃዎች፣ ለእያንዳንዱ ክፍል ተሟልተውለት መስተንግዶና የምግብ አገልግሎት ሳይጨምር ከነሙሉ ዕቃው ለእንግዶች የሚከራይ ተቋም ነው፤

**15.** "**Hotel Apartment**" shall mean an accommodation of food, drinking and as necessary entertainment, meetings, and similar services for tourists and other users, it is an institution where the guest cooks his own food in his own room;

**16.** "**Butcher's Shop**" shall mean an institution where drinks and food services including meat are sold;

**17.** "**Beverage**" shall mean alcoholic and non-alcoholic beverages, non-alcoholic beverages including coffee, hot and cold drinks;

**18.** "**Grocery**" shall mean an institution that provide an alcoholic and non-alcoholic beverage service;

**19.** "**Resort**" shall mean lodging of food, drinking and entertainment as needed, meeting and providing similar services to tourists and other users. However, there is a tourist attraction nearby;

**20.** "**Lounge**" shall mean a food service institution and places of entertainment open at night with music by bands or DJ music, providing food and drink service occasionally;

**21.** "**Guest House**" shall mean an institution that rents out a living room, a bedroom, cook house, bath parts and furniture all the equipment for each room, excluding accommodation of food services for guests;

፳፪ **"ፔንሲዮን"** ማለት የመኝታና እንደ አስፈላጊነቱ የቁርስ አገልግሎትን ለቱሪስቶችና ለሌሎችም ተጠቃሚዎች የሚያቀርብ ተቋም ነው፤

፳፫ **"ምግብ ቤት"** ማለት በባህላዊ ወይም በዘመናዊ ምግብና የመጠጥ አገልግሎት ለተጠቃሚ የሚያቀርብ የተሟላ የመመገቢያ ስፍራ ያለው ተቋም ነው፤

፳፬ **"የምሽት ክበብ"** ማለት በምሽት የሚከፈት የመዝናኛ ቦታዎች ሆኖ በቀጥታ የባንድ የሙዚቃ ዳንስ ወይም በዲጄ ሙዚቃ የሚቀርብበት፤ መዝናኛ ቦታ ያለውና የመጠጥ አልፎ አልፎም የምግብ አገልግሎት የሚያቀርብ ተቋም ነው፤

፳፭ **"ተገልጋይ"** ማለት የምግብ፤ የመጠጥ፤ የመኝታ እና የመዝናኛ አገልግሎቶችን ለመጠቀም ወደ ሆቴሎችና መሰል ተቋማት የሚሄዱ ተጠቃሚዎች ናቸው፤

፳፮ **"ባህላዊ መጠጥ ቤቶች"** ማለት አካባቢያዊ የማህበረሰብ ዕውቀትና ልምድን መሠረት ተደርጎ በአካባቢው ከሚገኙ ግብዓቶች የሚዘጋጁ የባህላዊ መጠጦች የሚሸጥባቸው ተቋም ናቸው፤

፳፯ **"ዓለም አቀፍ ይዘት ያላቸው ምግብ ቤቶች"** ማለት የተለያዩ ሀገራት ምግቦችና መጠጦችን በማዘጋጀት አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ነው፤

፳፰ **"የስብሰባ ማዕከል"** ማለት ለተለያዩ ዓለም አቀፍ፤ ሀገር አቀፍ ስብሰባዎች እና ሌሎች መሰል ኩነቶች የሚዘጋጁበት ተቋም ነው፤

22. "**Pension**" shall mean an institution that provides sleeping and as needed breakfast services to tourists and other users;

23. "**Restaurant**" shall mean an institution that provides to the user traditional or modern food and beverage service with a complete dining area;

24. "**Night Club**" shall mean a recreation area, a place of entertainment that opens at night where a band dances or DJs perform music an institution that provides drinks and food services occasionally;

25. "**Customer**" shall mean users who go to hotels and similar institutions to use food, drinking, sleeping accommodation and entertainment services;

26. "**Traditional Pubs**" shall mean an institution that sells local community knowledge and experience traditional drinks prepared from local ingredients;

27. "**Restaurants with International Content**" shall mean an institution that provides services by preparing drinks and foods of different countries;

28. "**Meeting Centre**" shall mean an institution where the various International, National meetings and other similar events are organized;

፳፱ **"ባርና ሬስቶራንት"** ማለት የተለያዩ የአልኮልና አልኮል የሌላቸው የመጠጥ ዓይነቶችን የሚያቀርብ እንዲሁም ውስን የምግብ አገልግሎት የሚሰጥበት ተቋም ነው፤

፴ **"ቁርስ ቤት ወይም ካፌ"** ማለት የተለያዩ ትኩስ መጠጦችን፤ ከአልኮል ነፃ የሆኑና የተዘጋጁ ቀላል ምግቦችን በማቅረብ አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ነው፤

፴፩ **"ቴክ አዌይ መሸጫ ወይም የጎዳና ላይ ተንቀሳቃሽ ምግብና መጠጥ አቅራቢዎች"** ማለት በጎዳናዎች ላይ ከቦታ ቦታ በመንቀሳቀስ ተጠቃሚዎች ይዘዋቸው የሚሄዱትን ምግብና መጠጦችን የሚያቀርቡ ናቸው፤

፴፪ **"የውጪ መስተንግዶ ወይም አውት ሳይድ ኬተሪንግ"** ማለት ለማህበራዊ ወይም ለንግድ አገልግሎት ምግብ፤ አልኮልና ከአልኮል ነፃ የሆኑ መጠጦችን አዘጋጅቶ የሚያቀርብ ተቋም ነው፤

፴፫ **"የበጋ ቤቶች"** ማለት በከተማ ዳርቻ በሚገኙ መናፈሻ ቦታዎች፤ በፓርኮችና በሐይቅ ዳርቻዎች ተሰርተው በሙቀት ጊዜ ወይም ዓመቱን ሙሉ ለተጠቃሚዎች አገልግሎት የሚሰጡ ቤቶች ናቸው፤

፴፬ **"ሆስቴል"** ማለት ለተማሪዎች፤ ለሠልጣኞች፤ ለአጥኚዎች፤ ለቡድን ተጓዦች፤ ለስፖርተኞች፤ ለቤተሰብ ተጓዦች ረዘም ላለ ጊዜ በግል ወይም በጋራ የማረፊያና ሌሎች ተያያዥ አገልግሎቶችን የሚሰጥ ተቋም ነው፤

፴፭ **"ሳውና ባዝ"** በደረቅ ሙቀት እጥበት የሚከናወንበት አነስተኛ የእንጨት ክፍል ወይም ቤት ነው፤

**29.** "**Bar and Restaurant**" shall mean an institution that offers a variety of alcoholic and non-alcoholic drinks and limited food service;

**30.** "**Breakfast House or Cafe**" shall mean an institution that provides various hot drinks, alcohol free services by providing simple and prepared meals;

**31.** "**Take Away Shop or Street Mobile Food and Beverage Vendors**" shall mean moving from place to place on the streets, they serve food and drinks users take it with them;

**32.** "**Outside Accommodation or Outside Catering**" shall mean an institution that provides food for a social or commercial use, prepare alcoholic and non-alcoholic drinks

**33.** "**Summer Houses**" shall mean houses that provide services to consumers in suburban parks, parks and by the lake shores done in heat time or the year full;

**34.** "**Hostel**" shall mean an institution that provides accommodation and other related services for students, trainees, researchers, group travellers, for sportsmen, for family travellers for longer periods alone or together;

**35.** "**Sauna Bath**" shall mean a small wooden room or home where dry heat washing is done;

፴፮ **"ስቲም ባዝ"** ማለት የእንፋሎት መታጠቢያ አገልግሎት በተሞላ ክፍል ውስጥ መቀመጥን የሚያካትት የስፓ ህክምና ሲሆን ይህም ውሃ በማሞቅ እና ወደ ክፍል ውስጥ በመልቀቅ በእንፋሎት መዝናናትንና የአተነፋፈስ ጤንነትን ለማሻሻል የሚረዳ እርጥበታማና ሞቅ ያለ አካባቢን በመፍጠር በጤንነት ማዕከሎችና በሆቴሎች የሚሰጥ የመዝናኛና የህክምና ክፍል ነው፤

፴፯**"ሎጅ"** ማለት በተፈጥሮ አካባቢዎች አቅራቢያ የሚገኝ በአካባቢው ቁሳቁሶች የተገነባ የምግብ፣ የመጠጥ፣ የመኝታ እና ሌሎች የመዝናኛ አገልግሎቶች የሚሰጥ ተቋም ነው፤

፴፰ **"የካምፕ አገልግሎት"** ማለት ለቱሪስቶች ለሌሎች ተግልጋዮች ጊዜያዊ የማረፊያ አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት ነው፤

፴፱ **"ቅድመ ምልከታ"** ማለት ተቋሙን ወይም ግለሰቡን በደንቡ ከተቀመጡት ሙያዊ መስፈርቶች አንጻር ማሟላቱን የማረጋገጥ ተግባር ነው፤

፵ **"አስተዳደራዊ እርምጃ"** ማለት በቢሮ፣ በክፍለ ከተማ ወይም በወረዳ ጽህፈት ቤት የሚወሰድ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ፣የገንዘብ ቅጣት፣ እሽጋ፣ እገዳ፣ ስረዛ እና መሰል እርምጃዎችን ያካትታል፤

፵፩ **"አስተዳደራዊ መቀጮ ደረጃዎች"** ማለት ተቋማት የህግ ጥሰት ሲፈጽሙ የሚቀጡትን አስተዳደራዊ መቀጮ ደረጃን የሚያመለክት ነው፤

፵፪ **"ሰው ሰራሽ ፀጉር"** ማለት በተፈጥሮ የራስ ያልሆነ ፀጉር ነው፤

36. "**Steam Bath**" shall mean a room equipped with a steam bath, a spa treatment that involves sitting in a room where the water is heated to relax and improve respiratory health by releasing steam by creating a humid and warm environment that helps in health centres and it is a recreational and medical department provided by hotels;

37. "**Lodge**" shall mean an institution provide services located near natural areas constructed from local materials that gives food, drinking, accommodation and other entertainment services;

38. "**Camping Service**" shall mean an organization that provide services accommodation of temporary sitting room for tourists and other customers;

39. "**Preliminary Observation**" shall mean the task of ensuring compliance with requirements of the institution or the individual from the prescribed professional;

40. "**Administrative Action**" shall includes actions a written warning, a fine, pack up prohibition, cancellation and the like by the Bureau, the Sub-City or the District Office;

41. "**Administrative Penalty Levels**" shall mean the levels of administrative fines when institutions commit violations of the law;

42. "**Synthetic Hair**" shall mean hair that is not natural hair;

፵፫ **"ማሳጅ"** ማለት አካላዊና አዕምሯዊ ጤናን ለመጠበቅ በሰለጠነ ባለሙያ የሚሰጥ ሰውነትን የማፍታታት አገልግሎት ነው፤

፵፬ **"ጂም"** ማለት አካላዊና አዕምሯዊ ጤናን ለመጠበቅ በባለሙያ ድጋፍ የሚሰራ ስፖርታዊ እንቅስቃሴ የሚደረግበት ቦታ ነው፤

፵፭ **"ሪዘርቬሽኒስት"** በሆቴል፣ በሪዞርት እና በሌሎች ተቋማት ውስጥ የሚሰራና ቀድመው የመኝታና የመመገቢያ ጠረጴዛ ለሚያሲዙ እንግዶች በተያዘላቸው ቦታ እንዲያርፉ የሚያደረግ፣ የስልክና የኢሜል ጥሪዎችን የሚቀበል፣ ስለ መኝታ ክፍሎች መረጃ የሚሰጥ፣ ክፍያዎችን የሚያካሂድ እና በተለያዩ ምክንያት የሚሰረዙ የተያዙ ማረፊያዎች እንዲሰረዙ ለማድረግ ኃላፊነት ያለው ባለሙያ ነው፤

፵፮ **"ቤል ቦይ"** በሆቴሎችና ሪዞርቶች ውስጥ የሚሰሩ ባለሙያዎች ሆነው ዋና ኃላፊነታቸውም እንግዶቹ ሲደርሱ ሰላምታ የሚሰጡ፣ ሻንጣቸውን በማገዝ ወደ ክፍላቸው የሚሸኙ፣ ስለ ሆቴሉ አገልግሎት መረጃ የሚሰጡ፣ የእንግዶቹን ሻንጣ የሚቆጣጠሩና በአጠቃላይ ለእንግዶቹ እገዛ የሚያደረጉ ባለሙያዎች ናቸው፤

**43.** "**Massage**" shall mean a massage given by a trained professional a service to loosen the body to maintain physical and mental health;

**44.** "**Gym**" shall mean a place for sports that works with professional support to maintain physical and mental health;

**45.** "**Reservationist**" shall mean who works in hotels, resorts and other institutions for guests who reserve a bed and dining table in advance makes sleepy, receives phone calls and emails, sleeps Sections that provide information, process payments and for various reasons the professional responsible for cancelling reserved accommodations;

**46.** "**Bell Boy**" shall mean as experts working in hotels and resorts their responsibility is to greet the guests when they arrive, help them with their luggage, room attendants, providing information about the hotel's services, they are experts who supervise and generally help the guests;

፵፯"ኮንሲያጅ" በሆቴሎች፣ ሪዞርቶች እና ሌሎች ተቋማት ውስጥ የሚሰሩ የእንግዳ ተቀባይ ባለሙያዎች ሆነው ዋና ኃላፊነታቸው ለተለያዩ ፍላጎቶችና ጥያቄዎች እንግዶችን መርዳት እንዲሁም ለምግብ ቤቶች ቦታ ማስያዣ፣ ለክስተቶች ትኬቶችን ማስያዝ፣ መጓጓዣን ማዘጋጀት፣ ስለአካባቢ መስህቦች ምክርን መስጠት፣ ስለ አካባቢው አጠቃላይ ጥያቄዎችን መመለስ፣ ከግል ረዳትነት ተግባራቸው በተጨማሪ የእንግዶችን ጥያቄዎችንና ቅሬታዎችን የሚቆጣጠር ባለሙያዎች ናቸው፤

፵፰"ዶር ማን" ማለት ሆቴሎች፣ ሬስቶራንቶችና በሌሎች ተቋማት ላይ የሚሰሩ እንግዳ ተቀባይ ባለሙያዎች ሆነው ዋና ኃላፊነታቸው እንግዶች ሲመጡ ሰላምታ በመስጠት ወደ ህንፃው ሲገቡ በሮችን ይከፍታሉ፣ ሻንጣዎችን ያግዛሉ፣ የምግብ፣ የመሰብሰቢያ እና የመሳሰሉትን አቅጣጫ ያሳያሉ፤ የተፈቀደላቸው እንዶች ብቻ ወደ ሆቴሉ እንዲገቡ የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለባቸው ባለሙያዎችን ያካትታል፤

፵፱"ሰው" ማለት የተፈጥሮ ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

፫ **የፆታ አገላለጽ**

በዚህ ደንብ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ጾታ ያካትታል፡፡

፬ **የተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ ደንብ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ በሚገኙ የሆቴልና መሰል አገልግሎት በሚሰጡ ተቋማት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

47. "**Concierge**" shall mean they are experts working in hotels, resorts and other institutions as receptionists of a guest, their main responsibility is to meet various needs and requests assisting guests and making restaurant reservations, for events, booking tickets, arrange transportation, advice on local attractions provide answer general questions about the area, in addition to their duties, are monitored personal assistance for the guests' questions and complaints;
48. "**Door Man**" shall mean those working in hotels, restaurants and other institutions as receptionists, their main responsibility is to greet guests when they arrive when entering the building by giving greeting, they open doors, help with luggage, they show the direction of restaurants, assembly and so on, it includes the experts responsible confirm for gusts only those who are allowed to enter into the hotel;
49. "**Person**" shall mean any physical or juridical person.

3. **Gender Expression**

In this Regulation, any expression in the masculine gender shall include the feminine gender.

4. **Scope of Application**

This regulation shall be applicable to hotels and similar service provider institutions in Addis Ababa City Administration.

፭ **ዓላማ**

የዚህ ደንብ ዋና ዋና ዓላማዎች የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

፩ በሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ውስጥ ለሚሰሩ ባለሙያዎች ወጥ የሆነ የአለባበስ፣ የጌጣጌጥ እና የመዋቢያ አጠቃቀም ሥርዓት መዘርጋት፣

፪ በሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ላይ የሚስተዋለውን ከኢትዮጵያዊ ባህልና እሴት ያፈነገጡ የአለባበስ፣ የጌጣጌጥ እና የመዋቢያ አጠቃቀምን ለማስተካከል፣

፫ በዘርፉ ተሰማርተው የሚሰሩ ሙያተኞች ሊደርስባቸው ከሚችለው አካላዊ፣ ሥነ ልቦናዊ ጫና እና አላስፈላጊ ጥቃቶችን ለመከላከል ናቸው፡፡

**ክፍል ሁለት**

**የሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋማትና ባለሞያዎች ዝርዝር**

፮ **ስለ ሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት**

ለዚህ ደንብ አፈጻጸም ሆቴልና መሰል አገልግለት መስጫ ተቋማት የሚከተሉት ናቸው፡-

፩ ሆቴልና መሰል አገልግለት መስጫ ተቋማት የሙያ ፈቃድ ወይም የንግድ ሥራ ፈቃድ ኖሯቸው ለቱሪስት ወይም ለሌሎች ተጠቃሚዎች አገልግሎት የሚሰጡ ሆቴል፣ ሆቴል አፓርትመንት፣ ሎጅ፣ ሪዞርት፣ ሞቴል፣ እንግዳ ማረፊያ፣ ሆስቴል፣ ፔንሲዮን፣ ሥጋ ቤት፣ ቁርስ ቤት ወይም ካፌ፣ የፈጣን ምግብ ወይም ቴክ አዌይ መሸጫ፣ ላውንጅ፣ ምሽት ክበብ፣ ባርና ሬስቶራንት፣ ምግብ ቤት፣ ግሮሰሪ፣ ሳውናና ስቲም ባዝ፣ ማሳጅ፣

5. **Objectives**

The main Objectives of this Regulation will be:

1. Establishing a system and procedure for standard dress out, the use of jewellery and cosmetics for experts working in hotels and similar service provider institutions;
2. To fix what is observed in hotels and similar service provider institutions from that deviates from Ethiopian clothing culture and values, use of jewellery and cosmetics;
3. To prevent physical, psychological pressure and unnecessary attacks on Experts who work in the field.

**PART TWO**

**THE LIST OF HOTEL AND SIMILAR SERVICE PROVIDER INSTITUTIONS AND LIST OF EXPERTS**

6. **Hotels and Similar Service Provider Institutions**

For the implementation of this regulation, hotels and similar service provider institutions are:

1. Hotel and similar service provider institutions professional license or business operation license those who have a license and provide services to tourists or other users hotel, hotel apartment, lodge, resort, motel, guest house, hostel, pension, butcher, breakfast house or cafe, fast food or take away Shop, lounge, night club, bar and restaurant, restaurant, grocery, sauna, steam bath, massage;

፪ ለቱሪስት የቱሪስት አገልግሎት የሚውሉ የበጋ ቤቶች፣ የካምፕ አገልግሎት፣ ዓለም አቀፍ ይዘት ያላቸው ምግብ ቤቶች፣ የምግብና፤ የመጠጥና የመዝናኛ አገልግሎት የሚሰጡ የስብሰባ ማዕከላት ፣ የቱሪስት መኪና አከራዮች እንዲሁም ሌሎች የቱሪስት አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት፤

፫ የባህላዊ መጠጥ ቤት እና የጀበና ቡና አገልግሎት መስጫ ተቋማት ናቸው፡፡

፯ **<u>የሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ የሙያ መስክ</u>**

ደንቡ ተፈፃሚ የሚሆንባቸው የሙያ መስኮች የሚከተሉት ናቸው፡-

፩ የእንግዳ አቀባበል የሙያ መስክ፡-

ሀ) በአየር ማረፊያ የሆቴል ተወካይ፣
ለ) የጥበቃ ሠራተኛ፣
ሐ) የሆቴል የእንግዳ አመላለሽ ሹፌር፣
መ) የዕለት ገንዘብ ተቀባይ፣
ሠ) እንግዳ ተቀባይ፣
ረ) ሪዘርቬሽኒስት፣
ሰ) የስልክ ኦፕሬተር ባለሙያ፣
ሸ) የህዝብ ግንኙነት ባለሙያ፣
ቀ) ኮንሲያጅ፣
በ) ቤልቦይ፣
ተ) ዶር ማን፣
ቸ) ፓርኪንግ ሠራተኛ፣
ኀ)የቢዝነስ ማዕከላት ሽያጭ ባለሙያ፣
ነ) የገበያና የሽያጭ ባለሙያ፣
ኘ) የኦዲት ክፍል ባለሙያ፣
አ) የሂሳብ ክፍል ባለሙያ፣
ከ) የሠው ሀብት ክፍል ባለሙያ፣
ወ) የቱሪስት ታክሲ አገልግሎት አሽከርካሪ፣ እና
ኸ) በየደረጃው የሚገኙ የእንግዳ አቀባበል ክፍል ኃላፊዎችን ያካትታል፤

2. Institutions providing services summer houses for tourist services, camping services, restaurants with international content, food beverage and entertainment services, convention centres, tourist car rental and other tourist services;
3. They are traditional pubs and coffee service institutions

7. **<u>Hotel and Similar Service Provider Career Field</u>**

The Career Fields to which the regulation applies are:

1. Hospitality Field of Operation:

a) Airport hotel representative;
b) Security guard;
c) Hotel Shuttle driver;
d) Daily Cashier;
e) Receptionist;
f) Reservationist;
g) Telephone Operator Specialist;
h) Public Relations Specialist;
i) Concierge;
j) Bell Boy;
k) Door Man;
l) Parking Attendant;
m) Business Centre Sales Expert;
n) Marketing and Sales Expert;
o) Audit Department Expert;
p) Accounting Department Expert;
q) Human Resource Department Expert
r) Tourist Taxi Service Driver; and
s) It includes Officials of the Reception Department at all levels.

፪ የቤት አያያዝ የስራ መስክ፡-

ሀ) የግቢ ውስጥ ጽዳት ባለሙያ፤

ለ) የእንግዳ ክፍል የፅዳት ባለሙያ፣

ሐ) የልብስ ንፅህና መስጫ ባለሙያ፤እና

መ) በየደረጃው የሚገኙ የቤት አያያዝ ክፍል ኃላፊዎችን ያካትታል፤

፫ የስፓ የስራ መስክ ፡-

ሀ) የማሳጅ ባለሙያ፤

ለ) የእስፓ እንግዳ ተቀባይ፤

ሐ) የስፓ ክፍል ባለሙያ እና

መ) በየደረጃው የሚገኙ የስፓ የስራ ክፍል ኃላፊዎችን ያካትታል፤

፬ የጂም የስራ መስክ፡-

ሀ) የአካል ብቃት አሰልጣኝ፤

ለ) የአካል ብቃት መስሪያ ቦታ ባለሙያ፤ እና

ሐ) በየደረጃው የሚገኙ የጂም የስራ ክፍል ኃላፊዎችን ያካትታል፤

፭ የጥገና ክፍል ባለሙያ ወይም የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ባለሙያ፤

፮ የምግብና መጠጥ ክፍል ባለሙያ፡-

ሀ) የምግብና መጠጥ አስተናጋጅ፤

ለ) የምግብና መጠጥ እንግዳ ተቀባይ፤

ሐ) የመኝታ ክፍል እና የምግብና መጠጥ ባለሙያ፤

መ) ባር ማን፤

ሠ) ረዳት ባር ማን፤

ረ) የባር ፅዳት፤ እና

ሰ) በየደረጃው የሚገኙ የምግብና መጠጥ መስተንግዶ ክፍል ኃላፊዎች ያካትታል፡፡

፯ በየደረጃው የሚገኙ የምግብ ዝግጅት ክፍል ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ናቸው፡፡

2. Housekeeping Field of Operation:
   a. Grounds Cleaner;
   b. Guest Room Cleaner;
   c. Clothes Cleaning Specialist; and
   d. It includes Housekeeping Department Heads at all levels.
3. Spa Field of Operation:
   a. Massage Therapist;
   b. Spa Receptionist;
   c. Spa Room Specialist; and
   d. It includes the Department Heads of the Spa at all levels.
4. Gym's Field of Operation:
   a. Fitness Trainer;
   b. Fitness Centre Specialist; and
   c. It includes the Heads of Gym Operations at all levels;
5. Maintenance Department Expert or Information Communication Expert;
6. Food and Beverage Department Specialist:
   a) Food and Beverage Host;
   b) Food and Beverage Receptionist;
   c) Bedroom and Food and Beverage Specialist
   d) Bar Man;
   e) Assistant Bar Man;
   f) Bar Cleaning; and
   g) It includes the Heads of the Food and Beverage Department at every level.
7. There are Officials and Experts in the Cooking Department at every level.

## ክፍል ሶስት

## ስለደንብ ልብስ አለባበስ፤ የጌጣጌጥ እና የመዋቢያ አጠቃቀም

**፰ ስለደንብ ልብስ አለባበስ**

፩ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፮) የተደነገገው የሙያ መስክ ባለሙያዎች የተፈቀደ የደንብ ልብስ አለባበስ የሚከተለው ይሆናል፡-

ሀ) እጅጌ ሙሉ ሸሚዝ እና ቁመቱ እስከ እግር ቁርጭምጭሚት የሚደርስ የጨርቅ ሱሪ፣ ወይም

ለ) ለሴቶች የጉርድ ቀሚስ ቁመቱ ከጉልበት በታች የሆነ እና ቅዱ ከጉልበት በላይ ያልሆነና ተላላፊ ወይም ተደራቢ የሆነ፣ ወይም

ሐ) ኮሌታ ያለው ወይም የሌለው ሙሉ ልብስ፣ ወይም

መ) ሰደሪያ በሸሚዝ ሆኖ ሙሉ የደረት ክፍልን የሚሸፍን ወይም ከአንገት በታች ያለውን የሰውነት ክፍል የሚሸፍን፣ ወይም

ሠ) ከጉልበት በታች የሆነ እና ቅዱ ከጉልበት በላይ ያልሆነ ወይም የደረት ክፍልን የሚሸፍን ከአንገት በታች ያለውን የሰውነት ክፍል የሚሸፍን ባህላዊ አልባሳት፣

ረ) ልሙጥ የሆነ፤ ጽሑፍ ወይም አርማ የሌለው ቀበቶ፣

ሰ) ሽፍን፤ የማያንሸራትት ሶል ያለው ጫማ ካልሲ ጋር ማድረግ፤

ሸ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከተራ ፊደል (ሀ) እስከ (ረ) ድንጋጌ ቢኖርም በየመኖሪያ አካባቢው የጀበና ቡና ፣ የባህላዊ መጠጥ ቤት እና ቴክ አዌይ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ሆነው የገቢ መጠናቸው ለዕለት ተዕለት ኑሮ የሚውል ተቋም ከሆኑ እንደሁኔታዉ ከአንገት በታችና ከጉልበት በላይ ያለዉን የሠውነት ክፍል የሚሸፍን ልብስ ብቻ መልበስ ይኖርባቸዋል፤

## PART THREE

## ABOUT UNIFORM DRESS OUT, THE USE OF JEWELLERY AND COSMOTICS

**8. About Uniform Dress Out**

1. The operational field stipulated in Sub article (1) and (6) of Article 7 of this regulation, the permitted uniform dress out for experts shall be:

a) A shirt with full sleeves and trousers of a cloth that reaches up to the ankles; or

b) For women, the skirt is below the knee and the slashed is not above the knee and which is infelicitous or overlapping; or

c) A full dress with or without a collar; or

d) A shirt that covers the entire chest or below the neck covering an existing body part; or

e) Below the knee and the slashed is not above the knee or a traditional garment that covers the chest and the body below the neck;

f) Smooth belt without text or logo;

g) Covered wear non-slip soles with socks;

h) In spite of the Provisions of letter (a) to (f) of this Sub Article, in each residence traditional coffee, traditional pub and take away service provider institutions whose income is used for daily living according to the situation, they should wear only covering clothing the part of the body below the neck and above the knee;

ቀ) የቱሪስት ታክሲ አሽከርካሪ እጅጌ ሙሉ ሸሚዝና እና ቁመቱ የእግር ቁርጭምጭሚት የሚሸፍን የጨርቅ ሱሪ ሳያርግ ወይም ምሽት ሲሆን በሸሚዙ ላይ አንፀባራቂ የቱሪስት ታክሲ አርማ ያለው ጃኬት ሳይለብስ አገልግሎት መስጠት፤

፪ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) የተዘረዘሩት ባለሙያዎች የተፈቀደ የደንብ ልብስ አለባበስ የሚከተለው ይሆናል፡-

ሀ) እጅጌው እስከ ክንድ የሚሸፍን ሸሚዝ እና ቁመቱ እስከ እግር ቁርጭምጭሚት የሚሸፍን የጨርቅ ሱሪ፣ ወይም

ለ) ሰደሪያ በሸሚዝ ሆኖ ሸሚዙ የደረት ክፍልን ወይም ከአንገት በታች ያለውን የሰውነት ክፍል የሚሸፍን፤

ሐ) ለሴቶች ጉርድ ቀሚስ ቁመቱ ከጉልበት በታች የሆነ እና ቅዱ ከጉልበት በላይ ያልሆነና ተላላፊ ወይም ተደራቢ የሆነ፤

መ) ልሙጥ የሆነ፣ ጽሑፍ ወይም አርማ የሌለው ቀበቶ ማድረግ፤

ሠ) ለቤት አያያዝ ባለሙያ ሽፍን፣ የማያንሸራትት ሶል፣ ከፍታ የሌለው የደህንነት መጠበቂያ ጫማ በካልሲ ማድረግ፤

ረ) ለልብስ ንጽህና መስጫ፣ ለማሳጅ እና ለስፓ ባለሙያዎች ሽፍን፣ የማያንሸራትት ሶል፤ ከፍታ የሌለው የደህንነት መጠበቂያ ጫማ በካልሲ ማድረግ፤

ሰ) ሁሉም የደንብ ልብሶች የሰውነት ክፍሎችንና ቅርፅን በጉልህ የማያሳዩ መሆን ይኖርባቸዋል፤

i) Tourist taxi driver with full shirt and long legs cloth trousers that cover the ankles without knitting or in the evening with the shirt, giving service without wearing a jacket with a reflective tourist taxi logo.

2. The uniform dress out for experts listed in Sub Article (2) and (3) of Article 7 of this regulation shall be:

a) A shirt with sleeves up to the arm and length up to the ankle covering trousers; or

b) The jumper that covers in the chest area or below the neck a part of the body;

c) For women, the knickers dress is below the knee and the slashed is not above the knee infelicitous or overlapping;

d) Wearing a belt that is smooth, without text or logos;

e) For housekeeping specialist coating, non-slip sole, non-slip safety wear slippers with socks;

f) Non-slip cover for clothes cleaners, massagers and spa specialists sol wearing low-top safety shoes with socks;

g) All uniforms should not prominently show body parts and shape they will have to.

፫ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀጽ (፬) የተዘረዘሩት ባለሙያዎች የተፈቀደ የደንብ ልብስ አለባበስ የሚከተለው ይሆናል፡-

ሀ) ሙሉ የስፖርት ቱታ፣

ለ) ከላይ የስፖርት ጃፖኒ ወይም የስፖርት ቲሸርት ሱሪው የስፖርት ቱታ፣

ሐ) ከላይ የስፖርት ጃፖኒ ወይም የስፖርት ቲሸረት ከስር ወይም ሱሪው/ የስፖርት ቁምጣ፣

መ) ከላይ የስፖርት ቱታ የስፖርት ቁመጣ፣

ሠ) ለስፖርት አገልግሎት የተፈቀደ ጫማ፤

፬ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀጽ (፭) የተዘረዘሩት ባለሙያዎች የደንብ ልብስ አለባበስ የሚከተለው ይሆናል፡-

ሀ) እጅጌ ሙሉ ቱታ ወይም የጥገና ባለሙያ ኮትና ሱሪ ቁመቱ የእግር ቁርጭምጭሚት የሚሸፍን መልበስ፣

ለ) ልሙጥ የሆነ፤ ጽሑፍ ወይም አርማ የሌለው ቀበቶ ማድረግ፤

ሐ) ሽፍን፤ የማያንሸራትት ሶል፤ የደህንነት መጠበቂያ የሆነ ጫማ በካልሲ ማድረግ፤

፭ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀጽ (፮) የተዘረዘሩ ባለሙያዎች የደንብ ልብስ አለባበስ የሚከተለው ይሆናል፡-

ሀ) ኮፊያ ወይም ፀጉር መሸፈኛ መጠቀም፤

ለ) እጅጌ ሙሉ ሸሚዝ እና ቁመቱ የእግር ቁርጭምጭሚት የሚሸፍን የጨርቅ ሱሪ በላዩ ላይ ሽርጥ መልበስ፤

ሐ) ለሴቶች የጉርድ ቀሚስ ቁመቱ ከጉልበት በታች የሆነ እና ቅዱ ከጉልበት በላይ ያልሆነና ተላላፊ ወይም ተደራቢ መልበስ፤

3. The uniform dress out for experts listed in Sub Article (4) of Article 7 of this regulation will be:
   a) Full sport tutus;
   b) Top sports jacket or sports t-shirt trousers sport tutus;
   c) Sports jacket or sports t-shirt underneath or trousers/ sports shorts;
   d) Top sport tutus, sport shorts;
   e) Shoes approved for sports use;
4. The uniform dress out for experts listed in Sub Article (5) of Article 7 of this regulation will be:
   a) Full-sleeved overalls or maintenance worker's coat and trousers with leg length wearing ankle coverings,
   b) Wearing a smooth belt without writing or logo;
   c) Cover, Non-slip sole, Safety shoes with socks to do.

5. The uniform dress out for experts listed in Sub Article (6) of Article 7 of this regulation attire will be:

   a) Wearing a hat or hair covering;
   b) Full sleeve shirt and ankle length cloth trousers to wear a garment over it;
   c) For women, the knickers dress is below the knee and the skirt is not above the knee infelicitous or layered clothing;

መ) ሽፍን፣ የማያንሸራትት ሶል፣ ከፍታ የሌለው የደህንነት መጠበቂያ ጫማ በካልሲ ማድረግ፣

ሠ) ሁሉም የደንብ ልብሶች የሰውነት ክፍሎችንና ቅርፅን በጉልህ የማያሳይ መሆን ይኖርበታል፡፡

፱ ስለ ጌጣጌጥ እና መዋቢያ አጠቃቀም

የተፈቀደ የባለሙያዎች የጌጣጌጥና ማስዋቢያ አጠቃቀም የሚከተለው ይሆናል፡-

፩ ለወንድ ባለሙያዎች የጌጣጌጥ እና መዋቢያ አጠቃቀም

ሀ) ፀጉር በአጭሩ የተቆረጠ እና የተበጠረ፣

ለ) የላይኛው ከንፈር ፂም ርዝመት ከከንፈሩ ጠርዝ ያልበለጠ ሆኖ ቀሪው ክፍል የሚላጭ ወይም የሚነሳ፣

ሐ) የተሸፈነ የአንገት ጌጥ፣

መ) ከጋብቻ ቀለበት ውጪ የእጅ ጌጥ አለመጠቀም፣

ሠ) ደማቅ ቀለም ያላቸው ብሬስ ወይም የጥርስ ማሰሪያ አለመጠቀም፣

፪ ለሴት ባለሙያዎች የተፈቀደ የጌጣጌጥ እና መዋቢያ አጠቃቀም

ሀ) ፀጉር በጉልህ በማይታይ የፀጉር ማስያዣ ወደ ኃላ ሰብስቦ ማሰር፣

ለ) የሚታሰረው የፀጉር ርዝመት የማጅራት እኩሌታን የማያልፍ፣

ሐ) የምታደርገው የአንገት ጌጥ በልብስ መሸፈን አለበት፣

መ) መጠኑ ትልቅ ያልሆነ፣ ተለጣፊ የሆነ እና በሁለቱም ጆሮ አንድ የጆሮ ጌጥ ማድረግ እና ከታችኛው የጆሮ ክፍል ውጪ የጆሮ ጌጥ ያለመጠቀም፣

ሠ) ከጋብቻ ቀለበት ወይም ከቃልኪዳን ቀለበት ውጪ የእጅ ጌጥ አለመጠቀም፣

d) Covered, non-slip sole, Safety shoes without height do it in socks;

e) All uniforms should not show body parts and shape prominently will have to.

## 9. The use of Jewellery and Cosmetics

The permitted use of jewellery and cosmetics for experts' shall be:

1. The use of jewellery and cosmetics for male experts:
   a) Hair cut short and braided;
   b) The length of the moustache of the upper lip does not exceed the edge of the lip and the remaining part removing or lifting;
   c) Covered necklace;
   d) Not wearing jewellery other than a wedding ring;
   e) Not using brightly colour braces or braces of the teeth.
2. The permitted use of jewellery and cosmetics for female experts:
   a) Tie the hair back with an inconspicuous hair tie;
   b) The length of the hair to be tied does not exceed the length of the scalp;
   c) The necklace she wear must be covered by clothing;
   d) Not large in size, sticky and one earring in both ears, wearing and not wearing earrings outside the lower part of the ear;
   e) Not wearing jewellery other than a wedding ring or engagement ring;

ረ) የእጅ ጥፍር በአጭሩ የተቆረጠ በንጽሕና የተያዘ፣

ሰ) ደማቅ ቀለም ያላቸው ብሬስ ወይም የጥርስ ማሰሪያ አለማድረግ፣እና

## ክፍል አራት

## ድጋፍና ክትትል፣ ቁጥጥር እና ኢንስፔክሽን

**፲ ድጋፍና ክትትል ስለማድረግ**

ቢሮው ወይም ጽህፈት ቤቱ የሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ፡-

፩ በዚህ ደንብ የተደነገጉትን የደንብ ልብስ አለባበስ፣ የጌጣጌጥ እና የመዋቢያ አጠቃቀም ጠብቀው እየሰሩ ስለመሆኑ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፣

፪ ዘርፉን ለማሳደግ በሚያደርጉት ጥረት የሚያጋጥማቸውን ችግሮች ለመፍታት የሚያግዝ የሙያ ምክር እና የአቅም ግንባታ ስልጣና ይሰጣል፣

፫ የሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ባለሙያዎች የደንብ ልብሰ አለባበስ፣ ጌጣጌጥ እና መዋቢያ አጠቃቀምን በተመለከተ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣

፬ የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች አክብረው ደረጃውን የጠበቀ አገልግሎት እየሰጡ ስለመሆናቸው መረጃ ለህዝብ ይፋ ያደርጋል፣ እውቅና ይሰጣል፡፡

**፲፩ ቁጥጥር ስለማድረግ**

፩ የሆቴልና መሰል አገልግሎት የተሰማራ ተቋም በደንቡ በተደነገገው የደንብ ልብስ አለባበስ፣ የጌጣጌጥ እና የመዋቢያ አጠቃቀም ሥርዓት መሠረት ሕግ አክብሮ እየሰራ ስለመሆኑ ቢሮው ወይም ጽህፈት ቤቱ ቁጥጥር ያደርጋል፣

f) Fingernails cut short and kept clean;

g) Not wearing brightly coloured braces or braces of the teeth;

## PART FOUR

## SUPPORT, SURVEILLANCE, SUPERVISION AND INSPECTION

**10. Support and Surveillance**

The Bureau or the Office, the hotel and similar service provider institutions:

1. To wear the uniform dress out, the use of jewellery and cosmetics prescribed in this regulation, provides support and surveillance to ensure usage is working properly;
2. To solve the problems they face in their efforts to grow the sector provides helpful career counselling and capacity building mandates;
3. surveillances performance regarding the Experts uniforms and dress out, use of jewellery and cosmetics of hotels and similar service provider institutions;
4. Complying with the provisions of this regulation and providing standard service information about them will be made public, it acknowledges.

**11. Supervision**

1. The Bureau or the Office will supervise whether an institution engaged in hotel and similar service provider is working in the uniform dress out, using jewellery and cosmetics procedure according to respect the law, the rules prescribed by the clothing regulation

፪ የሱፐርቪዥን ባለሙያ የቁጥጥር ሥራ ሲያከናውን ከሦስት ባለሙያ በታች ማነስ የለበትም፤

፫ የኢንስፔክሽን ሥራው በአንድ በጀት ዓመት ቢያንስ ለሁለት ጊዜ የሚሰራ ይሆናል፤

፬ የኢንስፔክሽን ባለሙያ የቁጥጥር ሥራን በሚመለከት ስለተደረሰበት ውጤት ለቢሮ ወይም ለጽህፈት ቤቱ ኃላፊ ፳፬ (ሃያ አራት) ሰዓት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በጽሁፍ ሪፖርት ያቀርባል፤

፭ ቢሮው ወይም ጽህፈት ቤቱ የሚመድባቸው ተቆጣጣሪዎች ወደ ሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ለቁጥጥር ተግባር ሲሄዱ ማንነታቸውን የሚገልጽ መታወቂያ እና ቁጥጥር ለማድረግ ከቢሮው የተሰጠ የተቆጣጣሪነት ልዩ መታወቂያ ማሳየት አለባቸው፤

፮ ተቆጣጣሪዎች ወደ ሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ለቁጥጥር ተግባር መሄድ ያለባቸው በመንግስት የሥራ ሰዓት ብቻ ነው፤

፯ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፮) የተደነገገው ቢኖርም ጥቆማ ሲደርስና አጠራጣሪ ሁኔታ ሲያጋጥም እና በቢሮው ወይም በጽህፈት ቤቱ ኃላፊ ሲታዘዝ በማንኛውም ሰዓት የቁጥጥር ሥራ ይከናወናል፤

፰ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፮) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከመንግስት የሥራ ሰዓት ውጪ ወደ ሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ለቁጥጥር ሥራ የሚሄዱ ከሆነ ከቢሮው ወይም ከጽህፈት ቤቱ ይህንኑ የሚያስረዳ ደብዳቤ መያዝ አለባቸው፡፡

2. When a supervisory expert performs supervisory work, there should not be less than three expertise;

3. The inspection works will be at least twice in one fiscal year;

4. The results of the inspection expert regarding the control work submits a written report to Bureau or the Head of the Office within 24 (twenty-four) hours;

5. The Bureau or the inspectors assigned by the Office to hotels and the service provider institutions that reveal their identity when they go for supervision special inspection issued by the Bureau to identify and control must show their Identity Card/ID;

6. Inspectors should go only during government working hours to hotels and similar service provider institutions for inspection;

7. Notwithstanding the Provisions of Sub Article (6) of this Article, when a suggestion is received and doubtful, when the situation arises and when ordered by the Bureau or the Head of the Office, in any case hours of operation will be supervised;

8. Subject to the Provisions of Sub Article (6) of this Article, the work of the government out of hours to hotels and similar service provider institutions for control work, if they are going, have a letter explaining the same from the Bureau or the Head of the Office they have to.

፲፪ **<u>ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ስለመስራት</u>**

በሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በደንቡ የተገለፀውን የደንብ ልብሰ አለባበስ፣ ጌጣጌጥ እና የመዋቢያ አጠቃቀም ሥርዓትን ለማስከበር ቢሮው ወይም ጽህፈት ቤቱ በየደረጃው ካሉ የአዲስ አበባ ከተማ ፖሊስ ኮሚሽን እና ከደንብ ማስከበር ባለሥልጣን ጋር በቅንጅትና በትብብር ይሠራል፡፡

፲፫ **<u>የሱፐርቪዥን ባለሙያ ተግባርና ኃላፊነት</u>**

የቢሮው ወይም የጽህፈት ቤቱ የሱፐርቪዥን ባለሙያ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡-

፩ የሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በደንቡ ላይ የተቀመጡትን መስፈርቶች ጠብቆ እየሰሩ መሆኑን የድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር ሥራ ያካከናውናል፣

፪ በሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የደንብ ልብስ አለባበስ፣ ጌጣጌጥና የመዋቢያ አጠቃቀምን በተመለከተ የማህበረሰቡን ባህላዊ እሴቶች የሚጣረሱ እና በባለሙያው ወይም በተጠቃሚው የግል ስብዕናን ወይም ሞራል ላይ ተጽእኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ተግባራት መኖሩ ጥቆማ ሲደርሰው ወይም በቁጥጥር ሥራ ላይ ሲያጋጥመው በዘህ ደንብ አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ (፯) መሠረት በማንኛውም ሰዓት ወደ ተቋሙ በመግባት ድርጊቱን ይቆጣጠራል፣ ማስረጃዎችን በፎቶግራፍ፣ በቪዲዮ እና በመሰል መረጃ መሰብሰቢያ መንገድ አደራጅቶ ከያዘ በኋላ በዚህ ደንብ መሠረት እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፣

12. **<u>Working in Coordination with Stakeholders</u>**

The uniform dress out, the use of jewellery and cosmetics of hotel and similar service provider institutions stated in the regulation, the Bureau or the Office to enforce the rules on or the Office at all levels works in coordination and cooperation with Addis Ababa City Police Commission and Code Enforcement Authority.

13. **<u>Duties and Responsibilities of the Supervisor</u>**

The supervisory expert of the Bureau or the Office will have the following duties and responsibilities:

1. Performs support, surveillance and supervise the work that hotel and similar service providers institutions are working in accordance with the requirements set forth in the regulation;
2. Regarding the uniforms, the use of Jewellery and cosmetics in hotels and similar service provider institutions, which violate the traditional values of the society and impact on the expert or user's personality or morale, when receiving a suggestion that there are activities can be carried out or in supervision work in accordance with Sub Article (7) of Article 11 of this regulation, in any case and time enters the facility and supervises the action; photograph evidence. After organizing it through photograph, video and similar information gathering methods take action or cause to be taken in accordance with this regulation;

፫ በቁጥጥር ሥራ ላይ ያከናወናቸውን ተግባራት እና ያጋጠሙ ችግሮች እንደአግባቡ ለቢሮው ወይም ለጽህፈት ቤቱ ኃላፊ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

**፲፬ <u>የሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ግዴታ</u>**

፩ የቢሮው የሱፐርቪዥን ባለሙያ ለድጋፍና ክትትል ወይም ለቁጥጥር ተግባር ወደ ሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ባአካል ተገኝቶ መረጃ ሲጠይቅ የሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋሙ ከሥራው ጋር ተያያዥነት ያላቸው መረጃዎችን የመስጠትና የመተባበር ግዴታ አለበት፤

፪ ቢሮው ወይም ጽህፈት ቤቱ የሚሰጠውን መጥሪያ ወይም የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ የመቀበል እና በጥሪው መሠረት በቢሮው ወይም በጽህፈት ቤቱ በአካል የመቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

**፲፭ <u>የአዲስ አበባ ከተማ ፖሊስ ኮሚሽን እና የደንብ ማስከበር ባለሥልጣን ሚና</u>**

የሆቴልና መስል አገልግሎት ስጪ ተቋማትን ላይ የአሰራር ወይም የደንብ ጥሰት ሲኖር ቢሮው ወይም ጽህፈት ቤቱ ለሚያከናነው ተግባር ድጋፍ ሲጠየቅ በየደረጃ ያለው የአዲስ አበባ ከተማ ፖሊስ ኮሚሽን ወይም የደንብ ማስከበር ባለሥልጣን ድጋፍ ያደርጋል፡፡

## <u>ክፍል አምስት</u>
## <u>ክልከላ፣ የደንብ ጥሰት እና ቅጣት</u>

**፲፮ <u>ክልከላ</u>**

ማንኛውም የሆቴልና መሰል አገልግሎት ተቋም፡-

፩ በዚህ ደንብ ክፍል ሦስት ስለደንብ ልብስ አለባበስ፤ የጌጣጌጥ እና የመዋቢያ አጠቃቀም ከተደነገገው ውጭ አገልግሎት መስጠት፤

3. According to the duties performed in the supervision work and the problems encountered, reports to the Bureau or the Head of the Office.

**14. <u>Duty of Hotels and Similar Service Provider Institutions</u>**

1. When the supervision expert of the Bureau physically present and asks for information related to the work from hotels and similar service provider institutions for support, surveillance or supervisory function, they must provide information and cooperate;
2. When the summons or warning letter issued by the Bureau or the Office, it is obligatory to accepting and appearing in person at the Bureau or the Office according to the summons.

**15. <u>Role of Addis Ababa City Police Commission and Code Enforcement Authority</u>**

The Addis Ababa City Police Commission or Code Enforcement Authority at every level, it supports when the Bureau or the Office is asked support for its work in violation of rules and regulations of hotels and similar service provider institutions

## <u>PART FIVE</u>
## <u>PROHIBITION, VIOLATION AND PENALITY</u>

**16. <u>Prohibition</u>**

Any Hotel and Similar Service Provider Institution:-

1. Providing services outside of the prescribed usage in part three of this regulation about uniform dress out , use of jewellery and cosmetic;

፪ ቢሮው ይህን ደንብ ለማስፈጸም በሚያወጣው መመሪያ እንደአግባብነቱ የሚወሰኑ ሌሎች ስለደንብ ልብስ አለባበስ፤ የጌጣጌጥ እና የመዋቢያ አጠቃቀም ውጭ አገልግሎት መስጠት፤

የተከለከለ ነው፡፡

**፲፯ <u>የደንብ ጥሰትን የሚያስከትሉ ድርጊቶች የቅጣት ደረጃ አመዳደብ</u>**

፩ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፰ እና ፱ የተደነገጉትን የደንብ ልብስ፣ ጌጣጌጥና የማስዋቢያ አጠቃቀም ጥፋት በሶሰት የጥፋት ደረጃ እንደሚከተለው የሚመደብ ይሆናል፡-

ሀ) ደረጃ "ሀ"፣

ለ) ደረጃ "ለ"፣ እና

ሐ) ደረጃ "ሐ" ናቸው፤

፪ በደረጃ “ሀ” ለተዘረዘሩ ጥፋቶች በሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ውስጥ ተግባራዊ ላላደረገ አገልግሎት ሰጪ ተቋም የቅጣት ደረጃ፤

ሀ) ደረት ክፍልን ያልሸፈነ ወይም ከአንገት በታች ያለውን የሰውነት ክፍል የሚሸፍን ሸሚዝ ያለበሰ፤

ለ) የሴቶች ጉርድ ቀሚስ ቁመቱና ቅዱ ከጉልበት በላይ ከሆነ፤

ሐ) በአነስተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ የሆቴልና መስል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በሸሚዝ ምትክ ቲሸርት ከለበሰ ከአንገት በታች ያለውን የስውነት ክፍል ካልሸፈነ፤

ሠ) ሰደሪያ ሆኖ በሸሚዝ ከተለበሰ ከአንገት በታች ያለውን የሰውነት ክፍል የማይሸፍን ከሆነ፤

ረ) ወንድ ባለሙያ የጆሮ ጌጥ ያደረገ ከሆነ፤

ሰ) የእጅ ጥፍር በንጽሕና ያልተያዘ ከሆነ፤

2. Those determined as appropriate by the directive issued by the Bureau and others to enforce this regulation, it is prohibited providing services outside of about uniform dress out, use of jewellery and cosmetic;

**17. <u>Allocation of Penalties for Actions that Cause Violation of Regulation</u>**

1. The usage of uniforms, jewellery and cosmetic stipulated in Article 8 and 9 of this regulation usage offense will be classified into three level of offense:
   a) Level "A";
   b) Level "B"; and
   c) Are Level "C".
2. For offenses listed in level "A" in hotels and similar service provider institutions penalty level for non-implementing service provider institution:

a. The part of the body that does not cover the chest or below the neck wearing a covering shirt;

b. If the height and length of the women's short dress is above the knee;

c. Small-scale hotel and similar service provider institutions, if he wears a t-shirt instead of a shirt, if it doesn't cover the part of the body below the neck;

d. If worn with a shirt if not covered the part of the body below the neck;

e. If a male expert wears earrings

ሸ) ለወንድ ባለሙያ በሚታዩ የሰውነት ክፍሎች ላይ ጌጣጌጦችን ያደረገ ከሆነ፤

ቀ) ለሴት ባለሙያ ከጆሮ ጌጥ ውጪ በሚታዩ የሰውነት ክፍሎች ላይ ጌጣጌጦችን ካደረገች፤

በ) ለምግብ ዝግጅት ባለሙያዎች ኮፊያ ወይም ፀጉር መሸፈኛ ካላደረገ፤

ተ) ከጉልበት በላይ የሆነ እና ቅዱ ከጉልበት በላይ የሆነ የደረት ክፍልን የማይሸፍን ወይም ወይም ከአንገት በታች ያለውን የሰውነት ክፍል የማይሸፍን ባህላዊ አልባሳት ያለበሰ፣

ቸ) እጅጌ ሙሉ ቱታ ወይም የጥገና ባለሙያ ኮትና ሱሪ ቁመቱ የእግር ቁርጭምጭሚት የሚሸፍን ልብስ ያላለበሰ ወይም ከዚህ በተቃራኒው ካለበሰ፣

ኀ) እጅጌ ሙሉ ሸሚዝ እና ቁመቱ የእግር ቁርጭምጭሚት የሚሸፍን የጨርቅ ሱሪ በላዩ ላይ ሽርጥ ያለበሰ የምግብና መጠጥ ባለሙያ፤

ነ) የቱሪስት ታክሲ አሽከርካሪ እጅጌ ሙሉ ሸሚዝና እና ቁመቱ የእግር ቁርጭምጭሚት የሚሸፍን የጨርቅ ሱሪ ሳያርግ ወይም ምሽት ሲሆን በሸሚዙ ላይ አንፀባራቂ የቱሪስት ታክሲ አርማ ያለው ጃኬት ሳይለብስ አገልግሎት መስጠት፣

አ) ሁሉም የደንብ ልብሶች የሰውነት ክፍሎችንና ቅርፅን በጉልህ የሚያሳይ ከሆነ፡፡

f. If fingernails are not kept clean;

g. If a male expert wears jewellery on body parts visible to;

h. For a female expert, if she does jewellery on visible parts of the body other than ear jewellery;

i. If food preparation expert do not wear hats or hair coverings;

j. The part of the chest that is above the knee and the chest is above the knee does not cover or cover the part of the body below the neck dressed in traditional clothes;

k. Full-sleeved overalls or repairman's coat and trousers with leg length, if he does not wear clothing that covers his ankles or vice versa;

l. Full sleeve shirt and ankle length trousers, a food and beverage expert not wearing a apron;

m. Tourist taxi driver with full shirt and full length leg cloth trousers that cover the ankles or in the evening with the shirt give away service without wearing a jacket with a reflective tourist taxi logo;

n. If all uniforms prominently display body parts and shapes.

፫. በደረጃ “ለ” ለተዘረዘሩ ጥፋቶች በሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ውስጥ ተግባራዊ ላላደረገ አገልግሎት ሰጪ ተቋም የቅጣት ደረጃ፡-

ሀ) ፀጉርን በአጭሩ ያልተቆረጠ እና ያላበጠረ ወንድ ባለሙያ ከሆነ፣

ለ) የላይኛው ከንፈር ፂም ርዝመት ከከንፈሩ ጠርዝ ያስበለጠ እና ቀሪው ክፍል ያልተላጨ ወይም ያላነሳው ከሆነ፣

ሐ) የአንገት ጌጥ ሳይሸፈን ቀርቶ የሚታይ ከሆነ፣

መ) ከጋብቻ ቀለበት ወይም ከቃል ኪዳን ቀለበት ውጪ የእጅ ጌጥ ያደረገ፣

ሠ) ደማቅ ቀለም ያላቸው ብሬስ ወይም የጥርስ ማሰሪያ የተጠቀመ፣

ረ) ፀጉር በጉልህ በማይታይ የፀጉር ማስያዣ ወደ ኃላ ሰብስባ ያላሰረች ሴት ባለሙያ ከሆነች፣

ሰ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ተራ ፊደል (ረ) መሠረት የሚታሰረው የፀጉር ርዝመት የማጅራት እኩሌታን ያለፈ ከሆነ፣

ሸ) መጠኑ ትልቅ የሆነ፣ ተለጣፊ የሆነ እና በሁለቱም ጆሮ አንድ የጆሮ ጌጥ ማድረግ እና ከታችኛው የጆሮ ክፍል ውጪ የጆሮ ጌጥ መጠቀም፡፡

ቀ) ከቤት አያያዝ፣ ከላውንደሪ፣ ከማሳጅ እና ስፓ ባለሞያዎች በስተቀር እጅጌ ሙሉ ሸሚዝ ካልለበሰ፣

፬. በደረጃ “ሐ” ለተዘረዘሩ ጥፋቶች በሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ውስጥ ተግባራዊ ላላደረገ አገልግሎት ሰጪ ተቋም የቅጣት ደረጃ፡-

ሀ) ልሙጥ የሆነ፣ ጽሑፍ ወይም አርማ የሌለው ቀበቶ አድርጎ አግልግሎት መስጠት፣

3. Penalty level for non-implementing service provider for offenses listed in level "B" in hotels and similar service provider institutions:

a) If he is a male expert whose hair is not cut short and not combed;

b) The length of the moustache of the upper lip exceeds the edge of the lip and the remaining part if he hasn't shaved or removed;

c) If the necklace is visible even if it is not covered;

d) Who wears jewellery other than a wedding ring or a promise ring;

e) Used brightly coloured braces or braces of the teeth;

f) A woman expert who does not tie her hair back with an inconspicuous hair tie;

g) The length of the hair to be tied according to ordinary letter (f) of this Sub Article, if it has passed a nape.

h) Large in size, sticky and wearing one earring in both ears and wearing earrings outside the lower part of the ear;

i) If he doesn't wear a full shirt except the laundry, housekeeping, massage and spa experts.

4. Penalty level for non-implementing service provider for offenses listed in level "C" in hotels and similar service provider institutions:

a) Give away service as wear a smooth belt without text or logo;

ለ) የቤት አያያዝ ወይም የስፓ ለልብስ ንጽህና መስጫ ወይም ለማሳጅ ወይም የምግብና መጠጥ ወይም የጥገና ክፍል ባለሙያ ሆኖ ሽፍን፣ የማያንሸራትት ሶል ያለው ጫማ ከካልሲ ጋር ሳያደርግ አግልግሎት መስጠት፤

ሐ) በየመኖሪያ አካባቢው የጀበና ቡና ፣ የባህላዊ መጠጥ ቤት እና ቴክ አዌይ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ሆነው የገቢ መጠናቸው ለዕለት ተዕለት ኑሮ የሚውል ተቋም ውስጥ አገልግሎት እየሰጡ ያሉ ሠራተኞች ከአንገት በታች ደረትንና ከጉልበት በላይ ያለዉን የሠውነት ክፍል የማይሸፍን ልብስ ለብሶ አግልግሎት መስጠት፤

ሰ) የጂም የስራ መስክ ባለሙያ ሆኖ ሙሉ የስፖርት ቱታ ሳያደረገ ወይም ከላይ የስፖርት ጃፖኒ ወይም የስፖርት ቲሸርት ሱሪው የስፖርት ቱታ ወይም ከላይ የስፖርት ጃፖኒ ወይም የስፖርት ቲሸረት ከስር ወይም ሱሪው ወይም የስፖርት ቁምጣ ወይም ከላይ የስፖርት ቱታ የስፖርት ቁመጣ ወይም ለስፖርት አገልግሎት የተፈቀደ ጫማ ሳያደርግ አግልግሎት ከሰጠ፡፡

**፲፰ አስተዳደራዊ ቅጣት**

ቢሮው ወይም ጽህፈት ቤቱ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጥፋት ፈጽሞ የተገኘን የሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋም ላይ አስተዳደራዊ ቅጣት ይጥላል፡-

፩ በደረጃ "ሀ"፤ "ለ" እና "ሐ" የተዘረዘሩት ጥፋቶች ፈጽሞ ሲገኙ ለመጀመሪያ ጊዜ እንዲያስተካክል የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፤

b) Housekeeping or spa for clothes cleaning or massage or as a food and beverage or maintenance department expert is serving with non-slip shoes with soles without socks;

c) The employees who are providing services in the institution of traditional coffee, traditional pub and take away in every residential area, their income is for daily living, wearing clothes that do not cover below the neck of the chest and the part of the body above the knees

d) As a gym expert without wearing a full sports sweat pants or above sports jacket or sports t-shirt trousers sports sweat pants or top sports jacket or sports t-shirt underneath or trousers or sports shorts or sports t-shirt or if he provides service without wearing shoes permitted for sports use.

**18. Administrative Penalty**

The Bureau or the Office will be imposed administrative fines on hotel and similar service provider institutions found the fault listed below:-

1. It will be given a written warning to make amends at Level "A"; "B" and "C" listed offenses for the first time ever;

፪ ማስጠንቀቂያ የተሰጠው አገልግሎት ሰጪ ተቋም ማሰጠንቀቂያ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ ፲፭ የሥራ ቀናት ውስጥ ካላሰተካከለ፡-

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ በአንቀጽ (፲፯) ንዑስ አንቀጽ (፪) በደረጃ "ሀ" ከተዘረዘሩ ጥፋቶች መካከል አንዱን የፈጸመ የሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋም ብር ፭ሺ.፻፻ (አምሳ ሺህ ብር) ይቀጣል፤

ለ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ተራ ፊደል (ሀ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከአንድ በላይ ጥፋቶችን ያጠፋ ተቋም ለያንዳንዱ ጥፋት ብር ፭ሺ.፻፻ (አምሳ ሺህ ብር) ተደምሮ ይቀጣል፤

ሐ) ማንኛውም ጥፋት የፈጸመ ተቋም ቅጣቱን ማስጠንቀቂያው በደረሰው ከ፲፮ኛው ቀን ጀምሮ ባሉት ፭ (አምስት) ተከታታይ የስራ ቀናት መክፈል አለበት፤

፫ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተራ ፊደል (ሐ) መሰረት ቅጣቱን ከፍሎ ጉድለቱን ካላስተካከለ ተጨማሪ ጊዜ መስጠት ሳያስፈልግ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለ፲፭ ቀን እንዲታገድ ይደረጋል፤ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካላስተካከለ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱ ይሰረዛል፤

፬ በደረጃ "ለ" በአንቀጽ ፲፯ ንዑስ አንቀጽ (፫) ከተራ ፊደል (ሀ) እስከ (አ) ድረስ የተደነገገውን ክልከላ ያላከበረና ማስጠንቀቂያ የተሰጠው አገልግሎት ሰጪ ተቋም ማሰጠንቀቂያ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ ፲፭ የሥራ ቀናት ውስጥ ካላሰተካከለ፡-

2. From the date of notification of the notified service provider institution if not corrected within 15 consecutive working days:

   a) IT will be fined Birr 50,000.00 (Fifty thousand Birr) if they are listed in level "A" in Article (17) Sub Article (2) of this regulation, a hotel and similar service provider institution that committed one of the offences;
   b) Subject to the Provision of ordinary letter (a) of this Sub Article, from one an institution that has committed more than one offense will be fined Birr 50,000.00 for each offense (Fifty thousand Birr) will be fined together;
   c) Any institution that has committed an offense and received the warning should paying in 5 (five) consecutive working days starting from the 16th day;

3. Paying the fine according to Sub Article (2) of this Article, if it does not correct the defect, it will be qualified without the need to give more time. License will be suspended for 15 days. If not fixed within the given time frame, the qualification certificate will be revoked.
4. In level "B" in Sub Article (3) of Article 17, from ordinary letter (a) to (n), a service provider institution that does not comply with the prescribed prohibition and has been warned within 15 consecutive working days from the date of notification, if not fixed:

ሀ) የሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋም ብር ፫ሺ.፻፻ (ሰላሳ ሺህ ብር) ይቀጣል፤

ለ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ተራ ፊደል (ሀ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከአንድ በላይ ጥፋቶችን ያጠፋ ተቋም ለያንዳንዱ ጥፋት ብር ፫ሺ.፻፻ (ሰላሳ ሺህ ብር) ተደምሮ ይቀጣል፤

ሐ) ማንኛውም ጥፋት የፈጸመ ተቋም ቅጣቱን ማስጠንቀቂያው በደረሰው ከ፲፮ኛው ቀን ጀምሮ ባሉት ፭ (አምስት) ተከታታይ የስራ ቀናት መክፈል አለበት፤

፭ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) የተደነገገውን ቅጣት መሰረት ቅጣቱን ከፍሎ ጉድለቱን ካላስተካከለ ተጨማሪ ጊዜ መስጠት ሳያስፈልግ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለ፲፭ ቀን እንዲታገድ ይደረጋል፤ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካላስተካከለ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱ ይሰረዛል፤

፮ ቢሮው ወይም ጽህፈት ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፫) እና (መ) መሠረት የወሰደውን ፈቃድ የመሰረዝ አስተዳዳራዊ እርምጃ ለሚመለከተው የንግድ ፈቃድ ሰጪ አካል የብቃት ማረጋገጫው እንደተሰረዘ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡

፯ በደረጃ "ሐ" በአንቀጽ ፲፯ ንዑስ አንቀጽ (፬) ከተራ ፊደል (ሀ) እና (ለ) የተደነገገውን ክልከላ ያላከበረና ማስጠንቀቂያ የተሰጠው አገልግሎት ሰጪ ተቋም ማሰጠንቀቂያ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ ፲፭ የሥራ ቀናት ውስጥ ካላሰተካከለ፡-

a) Hotel and similar service provider institution will be punished Birr 30,000.00 (thirty thousand Birr);

b) Subject to the Provision of ordinary letter (a) of this Sub Article, from one an institution that has committed more than one offense will be fined Birr 30,000.00 (thirty thousand Birr) will be fined together;

c) Any institution that has committed an offense and received the warning should paying in 5 (five) consecutive working days starting from the 16th day.

5. Pay the fine according to the penalty stipulated in Sub Article (4) of this Article, if it does not correct the defect, it will be qualified without the need to give more time. License will be suspended for 15 days. If not fixed within the given time frame, the qualification certificate will be revoked.

6. The Bureau or Office in accordance with Sub Article (3) and (d) of this Article, administrative action to cancel the license taken for the relevant business license. The issuing body must notify in writing that the certificate of qualification has been revoked.

7. In level "C" in Sub Article (4) of Article 17, from ordinary letter (a) and (b), a service provider institution that does not comply with the prescribed prohibition and has been warned within 15 consecutive working days from the date of notification. If not fixed:

ሀ) የሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋም ብር ፭ሺ.፻ (አምስት ሺህ ብር) ይቀጣል፤

ለ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ተራ ፊደል (ሀ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከአንድ በላይ ጥፋቶችን ያጠፋ ተቋም ለያንዳንዱ ጥፋት ብር ፭ሺ.፻ (አምስት ሺህ ብር) ተደምሮ ይቀጣል፤

ሐ) ማንኛውም ጥፋት የፈጸመ ተቋም ቅጣቱን ማስጠንቀቂያው በደረሰው ከ፲፮ኛው ቀን ጀምሮ ባሉት ፭ (አምስት) ተከታታይ የስራ ቀናት መክፈል አለበት፤

፰ ጥፋቱ የተፈጸመው በዚህ ደንብ አንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተራ ፊደል (ሸ) ላይ የተገለጸው ተቋም ከሆነ ብር ፩ሺ.፻ (አንድ ሺህ ብር) ይቀጣል፤ ጥፋቱ ከአንድ በላይ ሲሆን ለእያንዳንዱ ጥፋት ብር ፩ሺ.፻ (አንድ ሺህ ብር) ተደምሮ ይቀጣል፤

፱ ቢሮው ወይም ጽህፈት ቤቱ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (፪) እስከ (፰) የተደነገገውን አስተዳደራዊ ቅጣት ያልከፈለ የሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋሙን ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ቅጣቱን እስከነወለዱ እንዲከፍል ክስ ሊመሰርት ይችላል፤

፲ ማንኛውም ጥፋት የፈጸመ ሆቴል ወይም መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋም የተጣለበትን ቅጣት አጠናቆ ከፍሎና ስህተቱን አስተካክሎ ወደ ስራ ለመመለስ ጥያቄ ካቀረበ በተጨማሪ ብር፩ሺ.፻፻ (አስር ሺህ ብር) ቅጣት እንዲከፍል በማድረግ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አውጥቶ እንዲሰራ ይፈቃድለታል፤

a) Hotel and similar service provider institution will be punished 5,000.00 (Five thousand Birr);

b) Subject to the Provision of ordinary letter (a) of this Sub Article, an institution that has committed more than one offense will be fined 5,000.00 (five thousand Birr) will be fined together;

c) Any institution that has committed an offense and received the warning should paying in 5 (five) consecutive working days starting from the 16th day.

8. If the offense was committed on the simple letter (h) of Sub Article (1) of Article 8 of this regulation, if it is the specified institution, it will be fined 1,000.00 (one thousand Birr). The damage from one if it is above, 1,000.00 (one thousand Birr) in total for each fault will be punished;

9. The Bureau or the Office under Sub Articles (2) to (8) of this Article, hotel and similar service provider institution who has not paid the prescribed administrative fine, sue the institution to the competent court to pay the fine with its interest;

10. Any hotel or similar service provider institution that commits an offense to complete the punishment and pay and correct the mistake and return to work. If he submits a request, he must pay a fine of 10,000 (ten thousand birr). By doing this, it will be allowed to work by issuing a qualification certificate;

፲፩ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፲) ድንጋጌ ቢኖርም በዚህ ደንብ አንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተራ ፊደል (ሸ) የተገለጹት ተቋማት ጥፋታቸው አስተካክለው እስከቀረቡ ድረስ ካለተጨማሪ ቅጣት ስራቸውን እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡

**፲፱ <u>ስለ ቅሬታ አቀራረብ</u>**

፩ በዚህ ደንብ ድንጋጌዎች መሰረት በሚሰጥ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው ቅታውን በየደረጃው ለሚገኝ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔው በተሰጠው (፲) የስራ ቀናት ውስጥ በፅሑፍ ማቅረ.ብ ይችላል፤

፪ ቅሬታው የደረሰው የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ቅሬታው በደረሰው ፭ (አምስት)ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ የውሳኔ ሀሳቡን አዘጋጅቶ በየደረጃው ለሚገኘው የበላይ ኃላፊ ማቅረብ አለበት፤

፫ የውሳኔ ሀሳብ የቀረበለት ኃላፊ በአምስት (፭) የስራ ቀናት ውስጥ ውሳኔውን በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፤ የሚሰጠው ውሳኔም በመስሪያ ቤቱ ደረጃ የመጨረሻ ይሆናል፤

፬ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተደነገገው ቢኖርም በተሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወይም ምላሽ ያልተሰጠው ማንኛውም አገልግሎት ሰጪ አቤቱታውን ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡

11. Notwithstanding the Provisions of Sub Article (10) of this Article, Article 8 of this regulation, Sub Article (1) ordinary letter (h) of the mentioned institutions to correct their mistakes until they submit, they will be forced to do their jobs without further punishment.

**19. <u>Grievance Procedure</u>**

1. Any person aggrieved by a decision made under the provisions of this regulation, can be submitted in writing within (10) days the decision was given to the grievance committee at each level;
2. The complaint was received by the grievance committee in 5 (five) consecutive working days, it prepares the proposal and sends it to the higher curator at each level;
3. The curator to whom the proposal was submitted will make the decision within five (5) consecutive working days must be notified in writing. The decision is final at the Office level;
4. Notwithstanding the Provisions of Sub Article (3) of this Article, according to the decision, any service provider who has not responded to the complaint can submit it to a court of competent jurisdiction.

## ክፍል ሰድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፳ ስለ ተጠያቂነት**

፩. የሱፐርቪዥን ባለሙያ ወይም የቢሮው ወይም ጽህፈት ቤት ሠራተኛ ወይም ኃላፊ የተለየ ጥቅም ለማግኘት ወይም በወዳጅነት ወይም በዝምድና ወይም አግባብ ባልሆነ ሌላ ማንኛውም ግንኙነት በዚህ ደንብ ከተደነገገው ውጭ የሰራና እርምጃ እንዳይወሰድበት የተከላከለ፣ መረጃ የደበቀ አግባብባለው በወንጀል ሕግ ድንጋጌ ወይም በፍትሐብሄር ወይም በመንግሥት ሠራተኛ ሕግ ወይም በሁሉም ተጠያቂ ይሆናል፣

፪ ማንኛውም ሰው የዚህን ደንብ አፈጻጸም ያሰናከለ ወይም ያስተጓጎለ ከሆነ አግባብ ባለው ሕግ መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

**፳፩ የመተግበር ግዴታ**

ማንኛውም መንግስታዊ ወይም መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ወይም ግለሰብ ይህንን ደንብ በማክበርና በማስከበር ረገድ የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

**፳፪ ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች**

ይህንን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብና ካቢኔ ያወጣው መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

**፳፫ ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ ሰኔ ፳፩ ቀን ፪ሺ፲፮ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሰኔ ፳፩ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም.**

**አዳነች አቤቤ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

## PART SIX

## MISCELLNEOUS PROVISIONS

**20. Liability**

1. A supervisory expert or an employee of Bureau or the Office, to get a special benefit or through friendship or relationship or in any other relationship, acted and acted outside the provisions of this regulation, if he is hidden information and protected from being measure taken shall be liable under the provisions of the criminal law or civil or public servant law or by all;
2. If anyone obstructs or disrupts the implementation of this regulation, he will be liable according to the appropriate law.

**21. Duty to Cooperate**

Any governmental or non-governmental institutions or individuals have obliged to cooperate in complying with and enforcing this regulation.

**22. Inapplicable Laws**

Any Regulation and Directives issued by Cabinet or Customary Practices shall have no effect as regards matters covered by this regulation.

**23. Effective Date**

This regulation shall enter into force as of this 29 day of June, 2024.

**Done at Addis Ababa, this 28th day of June 2024.**

**ADANECH ABEBE DESA**

**MAYOR OF ADDIS ABABA**